# ኡ! ብየ እጮሃለሁ!

ቀስ ብዬ ስናገር የሚሰማ ካጣሁ፣
መርዶ እንደሚያረዳ ኡ! ብየ እጮሃለሁ።

በጧት ተነስቼ በእግሮቼ እየኳተንኩ፣
አፋፍ ላይ ወጥቼ እየተመለከትኩ፣
ጣቶቼን ከትቼ ጆሮን እየወተፍኩ፣
የሚነቃ ቢገኝ ኡ! ብየ እጮሃለሁ።

ወደ ላይ ሰማዩን እግዜርን እያየሁ፣
ወደ ታች ቸነፈር ሰቆቃ እያስተዋልሁ፣
ጉብታ ላይ ቆሜ ኡ! ብየ እጮሃለሁ፣
ወገን ተሰባሰብ አብረህ እዘን እያልኩ።

ጋንቤላና አሶሳን ኡ! ብዬ እጣራለሁ፣
መተከል መተማን ሐዘን አረዳለሁ፣
ገንጥለው ቆራጠው ጠብሰው በሉህ እያልኩ።

ለባሮ ለሙገር ለአዋሽ እነግራለሁ፣
ለአባይ ለተከዜ ለጣና አረዳለሁ፣
ተንደርድረው መጥተው ሊወሩህ ነው እያልኩ።

ለአሮጊቷ እማሆይ ለጦቢያ እነግራለሁ!
ልጆችሽ አዋርደው ሊያጠፉሽ ነው እያልኩ!
ጡት ከመንከስ አልፈው ከትፈው በሉሽ እያልኩ!

አፋፉ ላይ ሆኘ ኡ! ብየ እጮሃለሁ!
ህሊና ጭንቅ ይዞት ያጣጥራል እያልኩ፣
ፍትህ ሞቷልና ቀብር ድረሱ እያልኩ።

ደጀ ሰላም ሆኘ እግዞታ አሰማለሁ፣
መስጊድ ተንበርክኬ ለአላህ እነግራለሁ፣
ጦቢያን ይቅር በላት ታደጋትም እያልኩ።

ለዋርካው ለአድባሩ ኡ! ብዬ እጮሃለሁ፣
ቅርንጫፍህ ከድቶ እጀታ ሆነ እያልኩ፣
ከምሳር ተስማምቶ ቆርጦ ጣለህ እያልኩ።

ከምሬ ነው!

"ታዲያ ጩሃ!" አትሉም ልቤ ይነግረኛል፣
የአገር ልጅ ሲዘፍኑ እስክስታ ያወርዳል፣
ሐዘን ሲቀመጡም አብሮ እንባ ያፈሳል።

ጆሮዬን ጠቅጥቄ ኡ! ብዬ እጮሃለሁ፣
ተቧጭራ ተቧጣ ጦቢያ አነሰች እያልኩ፣
ሞረሽ ተጠራራ ተሰባሰብ እያልኩ።

የፍትህ ያለህ! ስል ኡ ብዬ እጮሃለሁ!
ጦቢያ እጆቿን ታስራ ተመተረች እያልኩ፣
አይናችን እያየ ልጠፋ ነው እያልኩ።

ለድፍን ጦቢያ ሕዝብ ኡ! ብዬ እጮሃለሁ፣
አገርህ ተቆርሶ ተከትፎ አለቀ እያልኩ፣
ዘር የሚቆረጥም አውሬ በላህ እያልኩ!
በአንድነት ከትመህ ተከላከል እያልኩ።

ቀስ ብዬ ስናገር የሚሰማ ካጣሁ!
በጥኋት ተነስቼ ከአፋፍ እወጣለሁ፣
ጸሐይ እስኪወጣ ኡ! ብዬ እጮሃለሁ፣
ለድፍን ጦቢያ ሕዝብ መርዶን አረዳለሁ፣
አገርህ ተቆርሶ ተከትፎ አለቀ እያልኩ፣
ዘር የሚቆረጥም አውሬ በላህ እያልኩ፣
እጅ-ለጅ ተያይዘህ ከመጥፋት ዳን እያልሁ፣
ኡ! ብዬ ኡ! ብዬ ኡ! ብዬ እጮሃለሁ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ግንቦት ሁለት ሺህ ዓ.ም.